DESIGN WEEK ADDIS ABABA

ጥቅምት 25, 2016 ዓ.ም

በአፍሪካ ማዕከል ውስጥ ፈጠራ እና ዲዛይንን ማበረታታት

በአስቸኳይ የሚለቀቅ

ለመረጃ፡ ቅድስት +251901002311

**“ስድስተኛው የዲዛይን ሳምንት በአዲስ አበባ (DWAA)” ከሕዳር 3- ሕዳር 9 2016 ዓ.ም ድረስ ለዲዛይንወዳጆች የተለያዩ መልቲሚዲያ ተሞክሮዎችን በመያዝ ይከፈታል።**

አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ **- ሰኞ፥ ሕዳር 03 2016 ዓ.ም-** ድንቅ መልቲሚዲያ ከቀስተደመና፥ ከካልቸር ክለብ እና ዋትስአውት አዲስ ጋር ባለው አጋርነት መሠረት፤ በምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚው የፈጠራ ፌስቲቫል የሆነው “የዲዛይንሳምንት በአዲስ አበባ (DWAA)” በተለያዩ ዘርፎች ውስጥ ያሉ ፕሮግራሞችን በመያዝ እና ዘርፈ ብዙ የፈጠራባለሞያዎች እና የፕሮግራም አጋሮችን በማካተት ይከፈታል።

ሕዳር 3 - ሕዳር 9 2016 ዓ.ም ስድስተኛው ሀገርአቀፍ የፈጠራ ፌስቲቫል የሚካሄድበት ሳምንት ነው። ይህ ሁለገብዝግጅት በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ያሉ ፈጠራዎችን የሚያበረታታ ሲሆን፤ እነዚህም ኢንዱስትሪዎች ከሥነ ሕንጻእና የከተማ ፕላን ዲዛይን፥ የኢንዱስትሪ ነክ ዲዛይኖች እና ኢንተሪየር ዲዛይን፥ ቴክኖሎጂ፥ ፋሽን እና ጨርቃ ጨርቅ፥ምግብ እና ሥነ ምግብ፥ ዕይታዊ ተግባቦት እና አርት እና መልቲሚዲያን ሁሉ የሚያካትት ነው።

“የዲዛይን ሳምንት በአዲስ አበባ”ን ከመክፈት በተጨማሪ፥ ድንቅ ስቱዲዮ በሌ ሩዋንዳ ባለው የቀስተደመና ማሳያየሚገኘውን የመልቲሚዲያ ስቱዲዮውንም ሕዳር 05 2016 ዓ.ም ይከፍታል።

“የዲዛይን ሳምንት በአዲስ አበባ (DWAA)” ጸሐፊ እና የጥበባዊ ሥራዎች ዳይሬክተር በሆነችው መታሰቢያ ዮሴፍ በ2014 ዓ.ም ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ ሲመሠረትም ሥራ ፈጣሪዎች እና አዳዲስ ነገሮችን የሚሠሩ ሰዎች የሚገኙባቸውኢንዱስትሪዎች ሥራቸውን የሚያሳዩበት ዓለምአቀፍ መድረክ እንዲያገኙ እና አዲስ አበባ የዓለምአቀፍ ዲዛይን ዋናከተማ አድርጎ ማስተዋወቅን ለመደገፍ ነው። ከዚህም በተጨማሪ፥ ለኢትዮጵያ የእድገት ፈተናዎች መፍትሔ ይሆኑ ዘንድዲዛይንን ማዕከል ያደረጉ ፕሮጀክቶች እንዲተገበሩ የሚደግፍ ሲሆን፥ ይህንንም አካሄድ መታሰቢያ ዮሴፍ “እድገትንበዲዛይን” በማለት ትጠራዋለች። “የዲዛይን ሳምንት በአዲስ አበባ (DWAA)” 2015 ዓ.ም ላይ ከተጀመረም በኋላ በዱባይዲዛይን ሳምንት ወቅት በለንደን የዲዛይን ፌስቲቫል እና ዳውንታውን ዲዛይን ላይ መሳተፍ ችሏል። ከዚህም በተጨማሪ፥“የዲዛይን ሳምንት በአዲስ አበባ (DWAA)” የዓለም ዲዛይን ሳምንታት አባል ሲሆን፥ ይህም የዚህን እያደገ የሚገኝዓለምአቀፍ መድረክ ተደራሽነት ያሰፋዋል። ከዚህ በፊትም በአፍሪካ የሚገኙ የተለያዩ የዓለምአቀፍ ዲዛይን ሳምንትተቋማት በአዲስ አበባ በሚካሄደው የዲዛይን ሳምንት ላይ ተሳትፈዋል።

“የዲዛይን ሳምንት በአዲስ አበባ (DWAA)” ሁለገብ የሆነውን ፌስቲቫል ለመታደም ከዓለም ዙሪያ የተለያዩ ጎብኚዎችንየሚስብ ለኢትዮጵያ ልዩ የሆነ “መዳረሻ ዝግጅት” መሆን ችሏል።

በዚህ ዓመት፥ “የዲዛይን ሳምንት በአዲስ አበባ (DWAA)” የአፍሪካዊ ጥበብን እውነተኛ አቅም በሚያጎለብቱ ንግግሮች፥ወርክሾፖች፥ ልምምዶች እና ዝግጅቶች የፈጠራ ሥራዎችን ለሚሠራው ማኅበረሰብ ድጋፍ ማድረጉን ይቀጥላል።“የዲዛይን ሳምንት በአዲስ አበባ (DWAA)” እውን ሊሆን የቻለው ከሀገርአቀፍ እና ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር ባለንየትብብር አጋርነት ሲሆን፤ ይህም ከቀስተደመና፥ ድንቅ መልቲሚዲያ፥ ዳሽን ካልቸር ክለብ ፥ ቶሞካ ቡና፥ ገበታ

ወይን፥ አይቪ ላውንጅ፥ ማሪዮት ኤክስኪውቲቭ አፓርትመንቶች፥ አራዳ ቢራ፤ ሰላምታ መጽሔት፥ ዋትስ አውት አዲስ፥ ሊንክአፕ አዲስ፥ ኢሊት ኢቬንትስ እና ከሌሎችም አጋሮች ጋር ያለውን አጋርነት ያካትታል።




Ø ከሕዳር **3-** ሕዳር **9 2016** ዓ.ም ድረስ ያሉ ሙሉ መርሐግብሮች

ሰኞ፥ ሕዳር 03 2016 ዓ.ም 12 ሰዓት ማታ - 3 ሰዓት ማታ

ቪአይፒ መክፈቻ በሸራተን ለግዠሪ ኮሌክሽን

በግብዣ ብቻ

Ø ረቡዕ፥ ሕዳር **05 2016** ዓ.ም **12** ሰዓት ማታ **- 3** ሰዓት ማታ

ቪአይፒ ቅድመ ዕይታ በቀስተደመና ማሳያ/ድንቅ ስቱዲዮ፥ ቦሌ ሩዋንዳ

በግብዣ ብቻ

DESIGN WEEK ADDIS ABABA

ዘርፍ፡ ሥነ ሕንጻ / የከተማ ፕላን ዲዛይን፥ የኢንዱስትሪ ነክ ዲዛይኖች እና የቤት ውስጥ ዲዛይን፥ ቴክኖሎጂ፥ ፋሽን እናጨርቃ ጨርቅ፥ ምግብ እና ሥነ ምግብ፥ ዕይታዊ ተግባቦት፥ አርት እና መልቲሚዲያ

Ø ሐሙስ፥ ሕዳር **06 2016** ዓ.ም **12** ሰዓት ማታ **- 3** ሰዓት ማታ

ክፍት ኤግዚቢሽን በቀስተደመና ማሳያ/ድንቅ ስቱዲዮ፥ ቦሌ ሩዋንዳ

ለሕዝብ ክፍት

የወርክሾፕ ተሞክሮ

መጠጥ እየተጎነጩ መሣል

የተሳትፎ ዋጋ፡ 700 ብር

Ø ዓርብ፥ ህዳር **07 2016** ዓ.ም **12** ሰዓት ማታ **- 3** ሰዓት ማታ

ክፍት ኤግዚቢሽን በቀስተደመና ማሳያ/ድንቅ ስቱዲዮ፥ ቦሌ ሩዋንዳ

ለሕዝብ ክፍት

የማሳያ ተሞክሮ

የቦርሳ አሠራር ትዕይንት በአቢሲኒያ ሌዘር

የተሳትፎ ዋጋ፡ ነፃ

Ø ቅዳሜ፥ ሕዳር **08 2016** ዓ.ም **8፡30** ቀን **- 1** ሰዓት ማታ

የአዳዲስ ነገር ፈጣሪዎች ማዕድ በአይቪ ላውንጅ፥ በማሪዮት ኤክስኪውቲቭ አፓርትመንት

በግብዣ **+** ቦታ በማስያዝ ብቻ

Ø እሁድ፥ ሕዳር **09 2016** ዓ.ም **7** ሰዓት ቀን **- 12** ሰዓት ማታ

የዲዛይን ገበያ በቶሞካ ካፌ፥ ለገሃር ባቡር ጣቢያ

ለሕዝብ ክፍት

DESIGN WEEK ADDIS ABABA




ስለ ዝግጅቱ የበለጠ ለማወቅ

Visit:-https://www.designweekaa.com
Follow @design week. A.A on Facebook/ Instagram/ Twitter **#DWAA2023 #Design Lovers**
Find the Design Week Addis Ababa page on Facebook Contact designweekaa@gmail.com and design@dinktv.com for additional information. For RSVPs events@dinktv.com

**SCAN ME /** ስካን አድርጉኝ